XML Frequently Asked Question in Amharic

*FAQ Sections*

General

Users

Authors

Developers

Home

መግቢያ

ኤማላ ቢሉ

ኤማላ ተመም

ምእላደ ቃላት

ምንጮች

መነሻ ገጽ

# መግቢያ

ኤማላ ፥ ከእንግሊዘኛው (Extensible Markup Language) ስም የተወሰደ ቃል ነው ። ሌላኛው አማራጭ ኤክስ/ኤም/ኤል (XML) ነበረ ። ነገር ግን ላጻጻፍ አመቺ አይደለም ፤ ስለዚህ ኤማላ ። ይህ ስለኤማላ ተደጋጋሚ መጠይቅና ምላሽ (Frequently Asked Questions) ዝርዝር ነው ። የሚያተኩረው ኤማላ ላይ ብቻ ስለሆነ ፥ ያንባቢው ጥያቄ ስለሃቴማላ (HTML) ፥ ስለስክሪፕት ቋንቋ ፥ ስለፕሮግራም መጻፊያ ቋንቋ ወይም ስለሌላ ከሆነ ፥ ይህ ቦታ ትክክለኛ አይደለም ። ይህ ተደጋጋሚ መጠይቅና ምላሽ (ተመም) ፥ ፕሮግራም ጸሐፊዎች ፥ ኤማላ ተጠቃሚዎች እንዲሁም ፍላጎት ያላቸውን በሙሉ በምንጭነት ይረዳል የሚል እምነት አለ ። ለማሳሰብ ያህል ፥ ይህ ሥራ የኤማላ (XML) ደንብ አይደለም ።

## ምሥጋና

የሚከተሉት ሰዎች ለዚህ ሥራ አስተዋጽኦ አድረገዋል ። ቴሪ አለን (Terry Allen) ፥ ታም ቦርግማን (Tom Borgman) ፥ ቲም ብሬይ (Tim Bray) ፥ ሮቢን ከቨር (Robin Cover) ፥ ባብ ዱቻርም (Bob DuCharme) ፥ ክርስቶፈር ማደን (Christopher Maden) ፥ ኤቭ ሜለር (Eve Maler) ፥ መኮቶ ሙራታ (Makoto Murata) ፥ ፒተር ሙሬይ-ረስት (Peter Murray-Rust) ፥ ሊያም ኩይን (Liam Quin) ፥ ማይክል እስፐርበርግ-መኩይን (Michael Sperberg-McQueen) ፥ ጆል ዌበር

(Joel Weber) ፥ እና ብዙ የSIG አባላት እንዲሁም የዚህ ሰነድ አንባብያን ባለም-አቀፍ ደረጃ ። እርማት ፥ ተጨማሪ ነገር ፥ ወይም ጥያቄ ስለሰነዱ ካሎት ላዘጋጁ ይላኩ ። ጥያቄው ለየት ካለ ፥ ለተገቢው የዜና-መድረክ ያቀርቡ ዘንድ ማሳሰቢያው እነሆ ።

## በቅርብ የተደረጉ ለውጦች

የሰነዱ ሰአደ (DTD) ከDocBook SGML ወደ QAML XML ተቀይሯል ።

## ቅንብር

ይህ ተመም (FAQ)ባራት ክፍሎች ይከፈላል ። ሀ) አጠቃላይ ለ) ኤማላ ተጠቃሚዎች ሐ) ኤማላ ደራሲያ እንዲሁም መ)ሶፍትዌር ገንቢዎች ። በዚህ ተመም ስህተቶች ካሉ ወይም ትችት ካሎት ለተመም ጠባቂ በሚከተለው አድራሻ pflynn@ucc.ie ይጻፉ ። ስለኤማላ (XML) ደንብ አስተያየት ካሎት የW3C ገጽ ይጎብኙ ።

## ስርጭት

ይህ ሰነድ በተለያየ ቅርጽ ይሰራጫል ። ዝርዝሩ እነሆ ።

- በኤማላ መልክ የተዘጋጀ http://www.ucc.ie/xml/faq.xml ይህ ሰነድ በንባብ ቅርጽ ለመመልከት download in text mode ።
- በሃቴማላ (HTML) መልክ የተዘጋጀ http://www.ucc.ie/xml/index.html ።
- ባልተበረዘ ንባብ መልክ የተዘጋጀ http://www.ucc.ie/xml/faq.txt ።
- ለማተም A4PostScript ፥ A4PDF ፥ Letter PostScript ፥ Letter PDF ። እነዚህን ሰነዶች ለመቃኘት ከፈለጉ ፥ ፖስትስክሪፕት መቃኛ ፕሮግራም ፥ ፒ/ዲ/ኤፍ መቃኛ ፕሮግራም ።
- ተመሙን በእትም መልክ የሚፈልጉ US$10.00 ላዘጋጁ ከሰደዱ ይላክላቸዋል ። በቅድሚያ ግን ላዘጋጁ ሊጽፉ ይገባል ።

ይህ ሰነድ በተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉሟል ።

- በጃፓንኛ ፦
  http://www.fxis.co.jp/DMS/sgml/cafe/library/etc/xmlfaq.html [Murata Makoto]
- በስፓንሽኛ ፦
  http://slug.ctv.es/~olea/sgml-esp/xfaq15.html [Jaime Sagarduy]
- በኮሪያኛ ፦
  http://xml.t2000.co.kr/faq/index.html [Kangchan Lee]
- በቻይናኛ ፦
  http://zxd.webjump.com/xml.html [Neko]
  http://weblab.crema.unimi.it/xmlzh/XML_FAQ.htm [Jiang Luqin]
- በፈረንሳይኛ ፦
  http://www.gutenberg.eu.org/pub/GUTenberg/publications/HTML/FAQXML/faqxml-fr.html [Jacques André]
- በቼክኛ ፦
  http://zvon.vscht.cz/ZvonHTML/Translations/xmlFAQ/front_all.html [Miloslav Nic]
- ባማርኛ ፦
  http://www.senamirmir.com/xml/xml_amharic_faq/ [Abass Alamnehe]

...

smirmir@senamirmir.com
©Senamirmir Project, 2001